የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 29
ADDIS ABABA, 7th July, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፫/፪ሺ፲፭

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ...........................ገጽ ፲፬ሺ፯፻፹፰

## Content

Proclamation No. 1293/2023

A Proclamation to Ratify the Extradition Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkiye ……......................................................Page 14788

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፫/፪ሺ፲፭

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ግንቦት ፪ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአንካራ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአካሄደው ፲፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

### PROCLAMATION NO. 1293/2023

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE EXTRADITION TREATY BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TURKIYE**

**WHEREAS,** the Extradition Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkiye has been signed in Ankara, on the 10th May, 2022;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 19th ordinary session held on 16th Day of May, 2023;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፫/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Extradition Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkiye Ratification Proclamation No 1293/2023".

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ግንቦት ፪ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአንካራ የተፈረመው የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ፀድቋል፡፡

## 2. Ratification of the Agreement

The Extradition Treaty signed in Ankara on the 10th of May 2022 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkiye, is hereby ratified.

## ፫. የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊነት

የኢፌዴሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 3. Responsibility of the FDRE Ministry of Justice

The FDRE Ministry of Justice is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Treaty.

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, On this 7th Day of July, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**